“ይህ ሰነድ በHUD የተዘጋጀው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህ ሰነድ ተተርጉሞ እንዲደርስዎ የተደረገው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ሲባል ብቻ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የዚህ ሰነድ ቅጂ ነው፤ ኦፊሴላዊነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈጻሚነት የሚኖረው። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።”

**የዩናይትድ ስቴትስ የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት**
**(U.S. Department of Housing and Urban Development)**

# አመልካቾች/ተከራዮች መረጃ ተላልፎ እንዲሰጥ ስምምነታቸውን የሚገልጹባቸው ሰነዶች ፓኬጅ

**ይህ ፓኬጅ የሚከተሉትን ሰነዶች ያካተተ ነው፡-**

1. **HUD-9887/A Fact Sheet አስፈላጊ የሆኑትን ማረጋገጫዎች የሚያብራራ**
2. **Form HUD-9887 (በአመልካቹ ወይም በተከራዩ የሚፈረም)**
3. **Form HUD-9887-A (በአመልካቹ ወይም በተከራዩ እና በቤቱ ባለቤት የሚፈረም)**
4. **Relevant Verifications (በአመልካቹ ወይም በተከራዩ የሚፈረም)**

እያንዳንዱ ቤተሰብ የ9887/A የመረጃ ሰነድ፣ HUD-9887 ቅጽ እና የHUD-9887-Aን ቅጽ አንድ ቅጂ ማግኘት ይኖርበታል።

“ይህ ሰነድ በHUD የተዘጋጀው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህ ሰነድ ተተርጉሞ እንዲደርስዎ የተደረገው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ሲባል ብቻ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የዚህ ሰነድ ቅጂ ነው፤ ኦፊሴላዊነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈጻሚነት የሚኖረው። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።”

**HUD-9887/A Fact Sheet**

# እገዛ በሚደረግበት መኖሪያ ውስጥ ያሉ አመልካቾች እና ተከራዮች የሚሰጡትን መረጃ ማረጋገጥ

## የማረጋገጡ ሂደት የሚያካትታቸው ነገሮች

የመኖሪያ ቤት እገዛ ለማግኘት ቢያንስ 18 ዓመት የሞላቸው አመልካቾችና ተከራዮች እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተሰብ ራስ፣ የትዳር ጓደኛ ወይም የኑሮ አጋር እድሜያቸው ምንም ይሁን ምን ለባለቤቱ ወይም ለአስተዳደር ወኪሉ (O/A) ወይም ለሕዝብ መኖሪያ ቤቶች አጀንሲ (PHA) የመኖሪያ ቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (Department of Housing and Urban Development (HUD)) ባወጣው መስፈርት መሠረት የሚጠየቁትን መረጃዎች መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

የፌደራል ሕግ፣ የሚደረገው እገዛ በትክክል ጥም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሲባል እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ይጠይቃል። **ይህ መረጃ የሚረጋገጠው በሁለት መንገዶች ነው፡-**

1. HUD፣ O/A እንዲሁም PHA እርስዎ የሰጡትን መረጃ ሕዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ አንዳንድ ኤጀንሲዎች (ለምሳሌ፡- የማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration (SSA))፣ የደሞዝና የሥራ አጥነት ድጎማ ጥያቄ መረጃዎችን የሚያስቀምጡ የስቴት ኤጀንሲዎች እንዲሁም በጤናና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (Department of Health and Human Services’ (HHS)) ውስጥ የደሞዝ፣ የአዲስ ተሸከርካሪና የሥራ አጥነት ድጎማ መረጃዎች በሚያስቀምጠው የአዲስ ቅጥሮች ብሔራዊ ማውጫ (National Directory of New Hires (NDNH)) ዳታቤዝ) ዘንድ ካለው መዝገብ ጋር በማመሳከር ሊያረጋግጥ ይችላል። HUD (ብቻ) በቀረጥ ተመላሽዎ ላይ ያለውን መረጃ ከዩናይትድ ስቴትስ የአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎቶች (U.S. Internal Revenue Service (IRS)) ሊያረጋግጥ ይችላል። ቅጽ HUD-9887 ላይ ሲፈርሙ ይህ መረጃ እንዲሰጥ መስማማትዎን መግለጽዎ ነው። በዚህ ቅጽ ላይ ፈቃድ የተሰጠበትን መረጃ ማግኘት የሚችሉት HUD፣ O/A እና PHA ብቻ ናቸው።

2. O/A ለዚህ ዝግጅት ብቁ መሆንዎን እና የሚከፍሉትን ኪራይ መጠን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይኖርበታል። ቅጽ HUD-9887፣ ቅጽ HUD-9887-A እንዲሁም እርስዎን በሚመለከቱ የግለሰብ ማረጋገጫና የስምምነት ቅጾች ላይ ሲፈርሙ ይህ መረጃ ተላልፎ እንዲሰጥ ስምምነትዎን መግለጽዎ ነው። O/A እርስዎን በተመለከተ ሊያገኛቸው የሚችላቸው መረጃዎች ዓይነት በፌደራል ሕጎች የተገደበ ነው። የሚያገኙት የገቢ መጠን የሚከፍሉትን ኪራይ መጠን ለመወሰን ያግዛል። O/A ሪፖርት ያደረጓቸውን የገቢ ምንጮችዎን በሙሉ ያረጋግጣል። የተከራይ የኪራይ ክፍያን ለማስላት በሚደረገው ጥረት የሚገኘው የገቢ መጠን ተቀንሶ እንዲታሰብ የሚያደርጉ አንዳንድ የአበል ዓይነቶች አሉ።
   **ምሳሌ፡-** ወ/ሮ አንደርሰን ዕድሜያቸው 62 ነው። ዕድሜያቸው የሕክምና አበል እንዲያገኙ ብቁ ያደርጋቸዋል። በዚህ አበል መሠረት ዓመታዊ ገቢያቸው ላይ ማስተካከያ ይደረጋል። የወ/ሮ አንደርሰን የሕክምና ወጪ የሚከፍሉትን ኪራይ መጠን ለመወሰን ስለሚረዳ O/A እርሳቸው ሪፖርት የሚያደርጉትን የህክምና ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።
   **ምሳሌ፡-** አቶ ሃሪስ ዕድሚያቸው ቢያንስ 62 ስላልሞላ እንዲሁም የአካል ጉዳት ወይም የአቀም ማጣት ችግር ስለሌለባቸው የሕክምና አበል ለማግኘት ብቁ አይደሉም። የሕክምና አበል ለማግኘት ብቁ ስላልሆኑ የሕክምና ወጪያቸው በሚከፍሉት የኪራይ መጠን ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። በመሆኑም O/A አቶ ሃሪስን ስለ ሕክምና ወጪያቸው ምንም ዓይነት ነገር ሊጠይቃቸው አይችልም እንዲሁም የእርሳቸውን የህክምና ወጪ በሚመለከት ከሦስተኛ ወገን ጠይቆ ማረጋገጥ አይችልም።

## የደንበኞች መብት ጥበቃ

ለHUD የሚደርሰው መረጃ በፌደራል የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ (Federal Privacy Act) መሠረት የተጠበቀ ይሆናል። ለO/A ወይም PHA የሚሰጠው መረጃ ደግሞ በግዛቱ የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ መሠረት የተጠበቀ ይሆናል። የHUD፣ O/A እና PHA ሠራተኞች እነዚህን የስምምነት ቅጾች አላግባብ ቢጠቀሙባቸው ቅጣት ይጣልባቸዋል። በማረጋገጫው ወይም በድጋሚ ማረጋገጫው ሂደት ወቅት ቅጽ HUD-9887፣ ቅጽ HUD-9887-A ወይም የግለሰብ ማረጋገጫ ስምምነት ቅጽ ቢሰጥዎ መፈረም አያስፈልግዎትም። ቅጾቹን እቤትዎ ሊወስዷቸው ሊያነብቧቸውና ከመረጡት ሦስተኛ ወገን ጋር ሊወያዩባቸው ይችላሉ። O/A እነዚህን ቅጾች ለመፈረም ተመልሰው የሚመጡበትን ሌላ ቀጠሮ ይሰጥዎታል።

ባለብዎ አካል ጉዳት ምክንያት የስምምነት ቅጹን ማንበብ እና/ወይም መፈረም ካልቻሉ O/A በRehabilitation Act of 1973፣ Section 504 መሠረት ተስማሚ ዝግጅት ያደርግልዎታል። እንዲህ ያሉ ዝግጅቶች የሚከተሉትን ነገሮች ሊያካትቱ ይችላሉ፡- አመልካቹ ወይም ተከራዩ ያለበት የአካል ጉዳት ቅጾቹን ለመሙላት ቢሮ ድረስ መምጣት እንዳይችል የሚያግዱት በሚሆንበት ጊዜ ቤቱ ድረስ መሄድ፤ አመልካቹ ወይም ተከራዩ እርሱን/እርሷን ወክሎ የሚፈርም ሌላ ግለሰብ እንዲወክሉ ማድረግ፤ የማየት እክል ያለባቸው ግለሰቦች ሲሆኑ ዝግጅቱ በትላልቅ ፊደላት የተዘጋጀ ጽሑፍ፣ ብሬል ወይም የሚያነብላቸው ሰው ማመቻቸትን ሊያካትት ይችላል።

ለአካለ መጠን የደረሰ የቤተሰብዎ አባል በበቂ ምክንያቶች የተነሳ ቅጽ HUD-9887ን ወይም የግለሰብ ማረጋገጫ ቅጾቹን በወቅቱ መፈረም ሳይችል ከቀረ O/A የዘገየበትን ምክንያት እንዲሁም ተገቢ የሆነውን ፊርማ በተቻለ ፍጥነት ማግኘት የሚችልበትን እቅድ በማስፈር መዝገቡን ያስቀምጣል።

በእርስዎ የስምምነት ፈቃድ መሠረት O/A ማረጋገጫውን በማካሄድ የደረሰበትን ውጤት O/A ራሱ ሊነግርዎ ይገባል ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን በኩል እንዲያውቁት ይደረጋል። በHUD Handbook 4350.3 Rev. 1 መሠረት O/A የደረሰበትን ውጤት በተመለከተ ተቃውሞዎን የሚገልጹበት አጋጣሚ ሊሰጥዎ ይገባል። ይሁን እንጂ በቅጽ HUD-9887 ወይም ቅጽ HUD-9887-A መሠረት የተገኘውን መረጃ በተመለከተ HUD፣ O/A ወይም PHA የተገኘውን ውጤት ሊያሳውቅዎ ይችላል።

O/A ፋይሎችን የሚያስቀምጠው ምሥጢራዊነታቸውን ማስጠበቅ በሚቻልበት ሁኔታ መሆን አለበት። የተከራዮችን መረጃ ምሥጢር ሳይጠብቅ የቀረ ማንኛውም የO/A ሠራተኛ በግዛቱ የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ የአፈጻጸም ድንጋጌዎች መሠረት እና በHUDም አፈጻጸም መሠረትም እርምጃ ይወሰድበታል። በተጨማሪም በግዴለሽነት አያያዝ ወይም መረጃውን አላግባብ በመጠቀም ምክንያት የተነሳ የተበደለ አመልካች ወይም ተከራይ ለደረሰበት ጉዳት የፍትሐ ብሔር እርምጃ ወይም ሌላ ተገቢ የማካካሻ እርምጃ በሠራተኛው ላይ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይችላል።

HUD-9887/A፣ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የFact Sheet (የመረጃ ሰነድ) እንዲሁም የHUD-9887 እና HUD-9887-A ቅጾችን ቅጂ አግባብ ካለው የግለሰብ ስምምነት ቅጾች ጋር O/A መስጠት እንደሚጠበቅበት ይገልጻል። የሚደርስዎ ፓኬጅ የሚከተሉትን ሰነዶች ያካተተ ይሆናል፡-

1. **HUD-9887/A Fact Sheet፡-** የመኖሪያ ቤት እገዛ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያስገቡ ግለሰቦች የሚያቀርቡትን መረጃ ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን መስፈርት ይዘረዝራል። እንዲሁም ይህ የመረጃ ሰነድ በማረጋገጡ ሂደት ወቅት ግለሰቦች የሚያገኙትን የመብት ከለላ ይዘረዝራል።
2. **ቅጽ HUD-9887፡-** በመንግሥት መስሪያ ቤቶች መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲደረግ ይፈቅዳል።
3. **ቅጽ HUD-9887-A፡-** የተጠቃሚዎች መብት ከለላን ጨምሮ ከሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ጋር የተያያዙ መስፈርቶችን ይዘረዝራል።
4. **የግለሰብ ማረጋገጫ ስምምነት፡-** ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆናቸውን እና የሚያገኙትን ጥቅም መጠን ለመወሰን ይረዱ ዘንድ በአመልካቾች/ተከራዮች የተሰጡ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል።

## የስምምነት ቅጾቹን ሳይፈርሙ መቅረት የሚያስከትለው መዘዝ

ቅጽ HUD-9887፣ ቅጽ HUD-9887-A ወይም የግለሰብ ማረጋገጫ ቅጾችን ሳይፈርሙ መቅረት የሚያገኙት እገዛ እንዲከለከል (ለአመልካቾች) ወይም እገዛው እንዲቋረጥ (ለተከራዮች) ሊያደርግ ይችላል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ቅጽ HUD-9887 እና 9887-Aን ይመልከቱ።

አመልካች ከሆኑና በዚህ ምክንያት ከተከለከሉ O/A ጥያቄዎ ለምን ውድቅ እንደተደረገ ሊያስረዳዎና ውሳኔው ላይ ይግባኝ የሚጠይቁበት ዕድል ሊሰጥዎ ይገባል።

ተከራይ ከሆኑና የሚያገኙት እገዛ በዚሁ ምክንያት ከተቋረጠ O/A በኪራይ ውሉ ላይ የተቀመጠውን አሠራር መከተል ይኖርበታል። ይህም ከO/A ጋር መገናኘት የሚችሉበትን ዕድል መስጠትን ይጨምራል።

## በዚህ የመረጃ ሰነድ (Fact Sheet) ውስጥ የተካተቱ ፕሮግራሞች

- የኪራይ እገዛ ፕሮግራም (Rental Assistance Program (RAP))
- የኪራይ ድጎማ (Rent Supplement)
- ሴክሽን 8 የመኖሪያ ቤቶች እገዛ ክፍያ ፕሮግራሞች (በቤቶች አስተዳደር ቢሮ የሚካሄድ) (Section 8 Housing Assistance Payments Programs (administered by the Office of Housing))
- ሴክሽን 202 (Section 202)
- ሴክሽን 202 እና 811 PRAC (Sections 202 and 811 PRAC)
- ሴክሽን 202/162 PAC (Section 202/162 PAC)
- ሴክሽን 221(ዲ)(3) ከገበያ ወለድ ተመን በታች (Section 221(d)(3) Below Market Interest Rate)
- ሴክሽን 236 (Section 236)
- HOPE 2 የባለብዙ ቤተሰብ የሕንጻ ክፍል (ዩኒት) የቤት ባለቤትነት (HOPE 2 Home Ownership of Multifamily Units)

O/A የዚህን የHUD የመረጃ ሰነድ አንድ ቅጂ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ መስጠት ይኖርበታል። በቅጽ HUD-9887-A ላይ ያሉትን መመሪያዎች ተመልከቱ።

“ይህ ሰነድ በHUD የተዘጋጀው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህ ሰነድ ተተርጉሞ እንዲደርስዎ የተደረገው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ሲባል ብቻ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የዚህ ሰነድ ቅጂ ነው፤ ኦፊሴላዊነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈጻሚነት የሚኖረው። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።”

# መረጃ የሚሰጥበት ማሳወቂያና ስምምነት

## ለዩናይትድ ስቴትስ የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD)፣ ለባለቤትና ለአስተዳደር ወኪል (O/A) እንዲሁም ለሕዝብ መኖሪያ ቤቶች ኤጀንሲ (PHA)

**የዩናይትድ ስቴትስ የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት**
**የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ**
**የፌደራል የመኖሪያ ቤቶች ኮሚሽነር**

| | | |
|---|---|---|
| መረጃ እንዲሰጥ የሚጠይቀው የHUD ቢሮ (ባለቤቱየHUDን የመስክ ቢሮ ሙሉ አድራሻ፣ በማን ስም እንደሚጻፍ፦ ዳይሬክተር፣ የባለ ብዙ ቤተሰብ ቤቶች መምሪያ መስጠት ይኖርበታል)፦ | መረጃ እንዲሰጥ የሚጠይቀው O/A (ባለቤቱ የባለቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ መስጠት ይኖርበታል።)፦ | መረጃ እንዲሰጥ የሚጠይቀው PHA ((ባለቤቱ የPHAን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የዳይሬክተሩን ወይም አስተዳዳሪውን ማዕረግ መስጠት ይኖርበታል። ለዚህ ፕሮጀክት የPHA ባለቤት ወይም የPHA ኮንትራት አስተዳዳሪ ከሌለ አጠቃላዩ ሳጥን ላይ የX ምልክት ያድርጉ።)፦ |

**ለተከራዮች የተሰጠ ማሳሰቢያ፦ መረጃውን የጠየቁት ድርጅቶች የሚጠቀሱበት ከላይ ያለው ክፍት ቦታ ካልተሞላ እዚህ ቅጽ ላይ አይፈርሙ። ይህ ቅጽ እንደተሰጠዎ መፈረም አያስፈልግዎትም። ቅጹን ወደ ቤትዎ ይዘው ሊሄዱና ካነበቡት እንዲሁም ከመረጡት ሦስተኛ ወገን ጋር ከተወያዩበት በኋላ ከመኖሪያዎቹ ባለቤት/ሥራ አስኪያጅ ጋር ተነጋግራችሁ በወሰናችሁት ዕለት መጥተው ስምምነቱን መፈረም ይችላሉ።**

**ሥልጣን፦** የኮንሶሊዴትድ አፕሮፕሪዬሽን ሕግ 2004 ሴክሽን 217 (Pub L. 108-199)። ይህ ሕግ የሚገኘው 42 U.S.C.653(J) ላይ ነው። ይህ ሕግ HHS በNDNH “የመዛግብት ክምችትና ስብስብ ሲስተም” ውስጥ ያለውን መረጃ በአንድ የተወሰነ ፕሮግራም ውስጥ የታቀፉ ሰዎችን የቅጥርና የገቢ ሁኔታ ለማረጋገጥ ሲባል ለቤቶች አስተዳደርና ለከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) አሳልፎ መስጠትን እንዲሁም የግል መለያቸውን ካስወገዱ በኋላ የግለሰቦቹን የቅጥር ሁኔታና የገቢ ሪፖርት ማረጋገጥን የሚፈቅድ ሕግ ነው። መረጃው በHUD ጸሐፊ በኩል ለግል ባለቤት፣ ለአስተዳደር ወኪል እንዲሁም ለኪራይ ቤቶች እገዛ ኮንትራት አስተዳዳሪ ተላልፎ ሊሰጥ ይችላል።

በHousing and Community Development Act)፣ 1992፣ ሴክሽን 903 እንዲሁም በOmnibus Budget Reconciliation Act)፣ 1993፣ ሴክሽን 3003ን መሠረት አድርጎ የተሻሻለው የStewart B. McKinney የቤት አልባ እገዛ የማሻሻያ ሕግ (Stewart B. McKinney Homeless Assistance Amendments Act)፣ 1988፣ ሴክሽን 904። ይህ ሕግ የሚገኘው 42 U.S.C. 3544 ላይ ነው። ይህ ሕግ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን ፈቃድ የሚሰጠውን የስምምት ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠይቃል፦ (1) HUD እና PHA የደሞዝና የሥራ አጥነት ድጎማ ጥያቄን መረጃ ከሚይዙ የግዛቱ ኤጀንሲዎች ይህንን መረጃ እንዲጠይቁ እንዲሁም (2) HUD፣ O/A እና PHA ከአመልካቹ ወይም ተጠቃሚው ብቃት ወይም ከሚያገኘው ጥቅም መጠን ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለውን የደሞዝና የምንዳ (wage) መረጃ አጣርቶ ብቁ መሆን አለመሆኑን የመወሰን ኃላፊነት፤ (3) HUD ከዩናይትድ ስቴትስ የማኅበራዊ ደህንነት አስተዳደር (U.S. Social Security Administration (SSA)) እንዲሁም ከዩናይትድ ስቴትስ የአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት (U.S. Internal Revenue Service (IRS)) የተወሰነ የቀረጥ ተመላሽ መረጃ እንዲጠይቅ።

**ዓላማ፦** ይህን ቅጽ ሲፈርሙ HUD፣ ከላይ ስሙ የተጠቀሰው O/A እንዲሁም PHA በቅጹ ላይ ከተዘረዘሩት የመንግሥት ኤጀንሲዎች የገቢ መረጃ እንዲጠይቁ መፍቀድዎ ነው። HUD፣ O/A እንዲሁም PHA ለመኖሪያ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ መሆንዎን እንዲሁም እነዚህ ጥቅሞች በትክክለኛው መጠን መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ በዚህ መረጃ አማካኝነት የቤተሰብዎን ገቢ ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል። HUD፣ O/A እንዲሁም PHA ብቁ መሆንዎን እንዲሁም የሚያገኙት ጥቅም ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሉ ከእነዚህ ምንጮች ጋር የማነጻጸሪያ ኮምፒውተር ፕሮግራሞችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። በተጨማሪም ይህ ቅጽ HUD፣ O/A እና PHA በኮምፒውተር ንጽጽሩ የተገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ የደሞዝ፣ የአዲስ ቅጥር (W-4) እንዲሁም የሥራ አጥነት ጥያቄ መረጃን አሁን ካሉበት ቀጣሪ ወይም ከፊተኛዎቹ ቀጣሪዎችዎ እንዲጠይቁ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

**የሚገኘው መረጃ አጠቃቀም፦** HUD ያገኘውን የገቢ መረጃ በግል ገበና አጠባበቅ ሕግ (Privacy Act) 1974, 5 U.S.C. 552a መሠረት መጠበቅ ይገባዋል። O/A and PHAም እንዲሁ ያገኙትን የገቢ መረጃ አግባብ ባለው የግዛቱ የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ መሠረት የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

HUD፣ O/A እና PHA በዚህ የስምምነት ማሳወቂያ ላይ የሰፈረውን መረጃ ካገኙ በኋላ እገዛውን ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆንዎ ወይም የሚያገኙት እገዛ መጠን ገና እንዳልተወሰነና ገና መረጋገጥ እንዳለበት ብቻ ያሳውቁዎ ይሆናል።

የHUD፣ O/A እንዲሁም PHA ተቀጣሪዎች በዚህ ስምምነት ቅጽ መሠረት የተገኘውን የገቢ መረጃ ያለ ፈቃድ ይፋ ቢያወጡ ወይም አላግባብ ጥቅም ላይ ቢያውሉ ቅጣት ይጣልባቸዋል።

**የስምምነት ቅጹን መፈረም የሚኖርባቸው ወገኖች፦** ቢያንስ 18 ዓመት የሞላው እያንዳንዱ የቤተሰብዎ አባል እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተሰብ ራስ፣ የትዳር ጓደኛ ወይም የኑሮ አጋር ዕድሜያቸው ምንም ይሁን ምን በመጀመሪያ ማረጋገጫ ወቅትም ሆነ በድጋሚ ማረጋገጫዎቹ ወቅት የስምምነት ቅጹን መፈረም ይኖርባቸዋል። ለአካለ መጠን የደረሰ አዲስ ሰው ቤተሰቡን ሲቀላቀል ወይም የቤተሰቡ አባላት 18 ዓመት ሲሞላቸው ተጨማሪ ፊርማዎችን ማስገባት ያስፈልጋል።

በሚከተሉት ፕሮግራሞች ሥር እገዛ ለማግኘት ማመልከቻ ያስገቡ ወይም እገዛ የሚያገኙ ግለሰቦች ይህን የስምምነት ቅጽ መፈረም ይጠበቅባቸዋል፦

የኪራይ እገዛ ፕሮግራም (RAP) (Rental Assistance Program (RAP))

የኪራይ ድጎማ (Rent Supplement)

ሴክሽን 8 የመኖሪያ ቤቶች እገዛ ክፍያ ፕሮግራሞች (በቤቶች አስተዳደር ቢሮ የሚካሄድ) (Section 8 Housing Assistance Payments Programs (administered by the Office of Housing))

ሴክሽን 202 (Section 202)፣ ሴክሽን 202 እና 811 PRAC (Sections 202 and 811 PRAC)፣ ሴክሽን 202/162 PAC (Section 202/162 PAC) ሴክሽን 221(ዲ)(3) ከገበያ ወለድ ተመን በታች (Section 221(d)(3) Below Market Interest Rate)

ሴክሽን 236 (Section 236)

HOPE 2 የባለብዙ ቤተሰብ ዩኒት የቤት ባለቤትነት (HOPE 2 Home Ownership of Multifamily Units)

**የስምምነት ቅጹን ሳይፈርሙ መቅረት፦** የስምምነት ቅጹን ሳይፈርሙ ከቀሩ እገዛው ሊከለከል ወይም የመኖሪያ ቤት ጥቅማ ጥቅሙ ሊቋረጥ ይችላል። አንድ አመልካች በዚሁ ምክንያት ከተከለከለ ባለቤቱ ወይም የአስተዳደር ኤጀንቱ በHandbook 4350.3 Rev. 1 ላይ የሰፈረውን የማሳወቂያ የአሠራር ሂደት መከተል ይኖርበታል። አንድ ተከራይ በዚሁ ምክንያት የሚያገኘው እገዛ ከተቋረጠበት ባለቤቱ ወይም የአስተዳደር ወኪሉ በኪራይ ውሉ ላይ ያለውን የአሠራር ሂደት መከተል ይኖርበታል።

**ስምምነት፦ በHUD ለሚታገዙ የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች ብቁ መሆን አለመሆኔን ወይም የማገኘውን ጥቅም መጠን ለመወሰን ሲባል HUD፣ O/A ወይም PHA በዚህ ቅጽ ጀርባ ላይ ከተዘረዘሩት የፌደራል ወይም የግዛቱ ኤጀንሲዎች የገቢ መረጃ እንዲጠይቁና እንዲወስዱ የተስማማሁ መሆኔን እገልጻለሁ።**

**“የሚፈረመው የኪራይ ውሉ የእንግሊዝኛ ቅጂ ብቻ ነው።”**

## መረጃ የሚሰጡ ኤጀንሲዎች

የግዛቱ የደሞዝ መረጃ ሰብሳቢ ኤጀንሲዎች (State Wage Information Collection Agencies)፡፡ (HUD እና PHA)፡፡ ይህ ስምምነት የሚመለከተው ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ እገዛ የሚሰጥባቸው መኖሪያዎች ተጠቃሚ በሆኑበት ጊዜ ያገኙትን ምንዳ እና የሥራ አጥነት ድጎማ ብቻ ነው፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ የማኅበራዊ ደህንነት አስተዳደር (U.S. Social Security Administration) (HUD ብቻ)፡፡ ይህ ስምምነት የሚያገለግለው ከወቅታዊው W-2 ቅጽዎ ላይ ለሚገኘው ምንዳ እንዲሁም የግል መተዳደሪያ መረጃ ብቻ ነው፡፡

በጤናና በሰብኣዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (Department of Health and Human Services) የመዛግብት ሲስተም ውስጥ የሚገኘው የአዳዲስ ቅጥሮች ብሔራዊ ማውጫ (National Directory of New Hires)፡፡ ይህ ስምምነት የሚመለከተው ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ እገዛ የሚሰጥባቸው መኖሪያዎች ተጠቃሚ በሆኑበት ጊዜ ያገኙትን ምንዳ እና የሥራ አጥነት ድጎማ ብቻ ነው፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ የአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት (U.S. Internal Revenue Service) (HUD ብቻ)፡፡ ይህ ስምምነት የሚያገለግለው በወቅታዊ የቀረጥ ተመላሽዎ ላይ ለተካተተው መረጃ ብቻ ነው፡፡

ይህ ስምምነት በታክስ ተመላሽዎ ላይ የሰፈረውን የሚከተለውን መረጃ ብቻ የሚመለከት ይሆናል፡-

1099-S ከሪል ስቴት የንግድ ውሎች የሚገኝ ገቢ ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Proceeds from Real Estate Transactions)

1099-B ከሪል ስቴት ደላላዎች እና ለዋጮች የንግድ ውሎች የሚገኝ ገቢ ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Proceeds from Real Estate Brokers and Barters Exchange Transactions)

1099-A በመያዣነት የሚያገለግል ንብረትን በመያዝ ወይም በመልቀቅ የሚገኝ ተመላሽ መረጃ (Information Return for Acquisition or Abandonment of Secured Property)

1099-G የተወሰኑ የመንግሥት ክፍያዎች ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Certain Government Payments)

1099-DIV የትርፍ ክፍያዎች እና ክፍፍል ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Dividends and Distributions)

1099 INT የወለድ ገቢ ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Interest Income)

1099-MISC የተለያዩ ገቢዎች ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Miscellaneous Income)

1099-OID የመጀመሪያ ተከፋይ ቅናሽ ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Original Issue Discount)

1099-PATR (ከኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚገኝ ተቀራጭ ክፍፍል ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Taxable Distributions Received from Cooperatives)

1099-R የጡረታ ፕላን ተጠቃሚዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement for Recipients of Retirement Plans W2-G)

የቁማር አሸናፊዎች ሒሳብ መግለጫ (Statement of Gambling Winnings)

1065-K1 የሽርክና የገቢ ድርሻ፣ ክሬዲት፣ ተቀናሾች ወዘተ (Partners Share of Income, Credits, Deductions, etc.)

1041-K1 የተጠቃሚ የገቢ ድርሻ፣ ክሬዲት፣ ተቀናሾች ወዘተ (Beneficiary's Share of Income, Credits, Deductions, etc.)

1120S-K1 የባለ ድርሻ ያልተከፋፈለ ተቀራጭ ድርሻ ገቢ፣ ክሬዲት፣ ተቀናሾች ወዘተ (Shareholder's Share of Undistributed Taxable Income, Credits, Deductions, etc.)

ከእነዚህ ምንጮች የሚገኘው የገቢ መረጃ እገዛ ለሚደረግባቸው የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች መጀመሪያ ላይም ሆነ በቀጣይነት ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ መሆኔን ወይም ብቁ ሆኜ መቀጠል አለመቀጠሌን እንዲሁም የማገኛቸውን ጥቅሞች መጠን ለመወሰን ሲባል የሰጠሁትን መረጃ ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንደሚውል እገነዘባለሁ፡፡

የHUD ቢሮ፣ የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ (OIG) ወይም PHA (አግባብ ያለው አካል) እንዲሁም O/A የሚከተሉትን ነገሮች በተናጠል እስኪያረጋግጡ ድረስ ይህን ስምምነት መሠረት በማድረግ ስለ እርስዎ የተገኘውን መረጃ ተመርኩዞ ቤተሰብዎ የሚያገኘውን እገዛ ለማቋረጥ፣ ለመከልከል፣ ለጊዜው ለማቆም ወይም ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃ አይኖርም፡- 1) የገቢውን፣ የምንዳውን ወይም የሥራ አጥነት ድጎማውን መጠን፣ 2) እንደነዚህ ያሉትን ገቢዎች፣ ምንዳዎች ወይም ጥቅሞች በእርግጥ አግኝተው ለራስዎ ጥቅም እያዋሉ(ወይም አውለው) ከሆነ እና 3) እነዚህን ገቢዎች፣ ምንዳዎች ወይም ጥቅሞች ያገኙበት ወቅት ወይም ከምን ጋር በተያያዘ እንዳገኙ፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረት የተሰጠውን መረጃ ከሦስተኛ ወገን ለማረጋገጥ ሲባል የተፈረመው ስምምነት ቅጂ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (ለምሳሌ፡- ቀጣሪ)፡፡

HUD፣ O/A ወይም PHA በዚህ ስምምነት አማካኝነት በተረጋገጠው መረጃ መሠረት የተገኘውን ውጤት ለእርስዎ ወይም እርስዎ ለወከሉት ሦስተኛ ወገን ያሳውቃሉ እንዲሁም በHandbook 4350.3 Rev. 1 መሠረት በዚህ ውጤት ላይ ተቃውሞዎን ማሰማት የሚችሉበትን ዕድል ይሰጡዎታል፡፡

የስምምነት ቅጹን መፈረም የሚጠበቅበት አንድ የቤተሰብዎ አባል በበቂ ምክንያት በወቅቱ የስምምነት ቅጹን መፈረም ሳይችል ቢቀር O/A የዘገየበትን ምክንያት እንዲሁም ፊርማውን በተቻለ ፍጥነት ለማግኘት የወጣውን እቅድ አስፍሮ መዝገቡን ይይዛል፡፡

ይህ የስምምነት ቅጽ ከተፈረመ ከ15 ወር በኋላ አያገለግልም፡፡

---

**የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ መግለጫ፡፡** የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) በሚከተሉት ሕጎች መሠረት ይህንን መረጃ የመሰብሰብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡- U.S. Housing Act of 1937, ተሻሽሎ የወጣው (42 U.S.C. 1437 et. seq.)፤ the Housing and Urban-Rural Recovery Act፣ 1983 (P.L. 98-181)፤ Housing and Community Development Technical Amendments of 1984 (P.L. 98-479)፤ እንዲሁም Housing and Community Development Act፣ 1987 (42 U.S.C. 3543)፡፡ መረጃውን የሚሰበስበው HUD ሲሆን ዓላማውም የአመልካቹን ብቁ መሆን አለመሆን፣ የሚታሰበውን ዩኒት ስፋት እንዲሁም ተከራዩ(ዮቹ) ለኪራይና ለአገልግሎት ክፍያው መክፈል ያለባቸውን መጠን ለመወሰን ነው፡፡ HUD ይህንን መረጃ የሚጠቀምበት አንዳንድ የHUD ንብረቶችን በማስተዳደር ረገድ እገዛ ለማድረግ፣ የመስተዳድሩን የገንዘብ ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲሁም የተሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ HUD፣ ባለቤቱ ወይም የአስተዳደር ኤጀንቱ (O/A) ወይም የሕዝብ ቤቶች ኤጀንሲ (PHA) የሰጡትን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የኮምፒውተር ንጽጽር ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡ ይህ መረጃ አግባብ ላላቸው የፌደራል፣ የግዛቱ እና የአካባቢ ኤጀንሲዎች ሊላክ የሚችል ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለፍትሐ ብሔር፣ ለወንጀል ወይም ለተቆጣጣሪ መርማሪዎችና አቃቢያነ ሕግ ተላልፎ ሊሰጥ ይችላል፡፡ አለበለዚያ ግን ሕግ በሚፈቅደውና በሚጠይቀው መሠረት ካልሆነ በቀር መረጃው ከHUD ውጭ ላሉ ወገኖች ተላልፎ አይሰጥም፡፡ የተጠየቀውን መረጃ ሁሉ መስጠት ይጠበቅብዎታል፡፡ ማንኛውንም መረጃ ሳይሰጡ መቅረት ብቁ መሆንዎን የማረጋገጡ ሂደት እንዲዘገይ ወይም ውድቅ እንዲደረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

---

**ይህንን ስምምነት አላግባብ መጠቀም የሚያስከትለው ቅጣት፡-**

HUD፣ O/A እና ማንኛውም PHA (ወይም ማንኛውም የHUD፣ O/A ወይም PHA ተቀጣሪ) በዚህ ስምምነት መሠረት የተሰበሰበውን መረጃ ያለ ፈቃድ ይፋ አድርጎ ወይም አላግባብ ተጠቅሞ ቢገኝ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡

በቅጽ HUD 9887 መሠረት የተሰበሰበው መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው በቅጽ HUD 9887 ላይ ለተጠቀሱት ዓላማዎች ብቻ ነው፡፡ አንድን አመልካች ወይም ተከራይ የተመለከቱ መረጃዎችን በሐሰት እያወቀ ወይም ሆነ ብሎ የሚጠይቅ፣ የሚወስድ ወይም ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ ሕግ በመተላለፍ የሚከሰስ ሲሆን ከ5,000 ዶላር የማይበልጥ ቅጣት ይጣልበታል፡፡

በግዴለሽነት መረጃው ይፋ በመደረጉ ተበደልኩ ያለ ማንኛውም አመልካች ወይም ተከራይ ለደረሰው ጉዳት በHUD ሹም ወይም ሠራተኛ፣ በባለቤቱ ወይም መረጃው አላግባብ ይፋ እንዲሆን ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ባደረገው PHA ላይ የፍትሐ ብሔር ወይም ሌላ ተገቢ ሆኖ የተገኘው እርምጃ እንዲወሰድ መጠየቅ ይችላል፡፡

# አመልካቾች/ተከራዮች መረጃ ይፋ እንዲደረግ የሰጡት የስምምነት ቃል

## የመኖሪያ እገዛ ለማግኘት ያመለከቱ ግለሰቦች የሰጡትን መረጃ በተመለከተ ባለቤቶች የሚሰጡት ማረጋገጫ

**የዩናይትድ ስቴትስ የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት**
**የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ**
**የፌደራል የመኖሪያ ቤቶች ኮሚሽነር**

### ለባለቤቶች የተሰጠ መመሪያ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲፈርሙባቸው ለአመልካቾች/ተከራዮች ስጡ። በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሠረት በስቴፕለር ሽቦ ወይም በአግራፍ ያያይዟቸው።
   a. የHUD-9887/A የመረጃ ሰነድ (Fact Sheet)።
   b. ቅጽ HUD-9887።
   c. ቅጽ HUD-9887-A።
   d. ተዛማጅነት ያላቸው ማረጋገጫዎች (HUD Handbook 4350.3 Rev. 1)።

2. ለአመልካቾቹ እና ተከራዮቹ የሚከተሉትን ጉዳዮች በቃል አሳውቁ፡-
   a. እነዚህን ቅጾች ቤታቸው ወስደው ሊያነቧቸውና ከመረጡት ሦስተኛ ወገን ጋር ሊወያዩባቸው ከዚያም ከእናንተ ጋር በያዙት የቀጠሮ ዕለት ተመልሰው ሊፈርሙባቸው እንደሚችሉ እንዲሁም
   b. ማንኛውንም ስምምነት ለማንበብ እና/ወይም ለመፈረም የሚከለክል የአካል ጉዳት ካለባቸው እናንተ፣ እንደ ባለቤት፣ አመቺ የሆነ ዝግጅት ማድረግ እንደሚጠበቅባችሁ።

3. ባለቤቶች ተፈላጊውን የአመልካቾች/ተከራዮች ፊርማ(ዎች) ካገኙ በኋላ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የHUD9887/የመረጃ ሰነድ (Fact Sheet)፣ ቅጽ HUD-9887 እንዲሁም ቅጽ HUD-9887-A መስጠት ይጠበቅባቸዋል።በተጨማሪም ጥያቄ ከቀረበላቸው ባለቤቶች ለአመልካቾች/ተከራዮች የተፈረመባቸውን የግለሰብ ማረጋገጫ ቅጾች ቅጂ መስጠት ይኖርባቸዋል።

### ለአመልካቾች እና ተከራዮች የተሰጠ መመሪያ

ይህ፣ ቅጽ HUD-9887-A የተገለጋዩን መረጃ እንዲሁም ባለቤቶች ሊያከናውኑት የሚገባውንና HUD የሚጠይቀውን ማረጋገጫ የሚመለከት የመብት ጥበቃ ያካተተ ነው።

1. የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚያብራራውን ይህን ጽሑፍ ያንብቡ፡-
   - መረጃ መስጠትን በሚመለከት HUD ያስቀመጠው መስፈርት እንዲሁም
   - ሌሎች የተገልጋይ መብት ጥበቃዎች።
2. የሚከተለውን በማረጋገጥ መጨረሻው ገጽ ላይ ይፈርሙ፡-
   - ቅጹን እንዳነበቡ ወይም
   - ባለቤቱ ወይም የመረጡት ሦስተኛ ወገን እንዳብራራልዎ እንዲሁም
   - ለተዘረዘረው ዓላማ ሲባል መረጃ ተላልፎ እንዲሰጥ መስማማትዎን

### አመልካቾች/ተከራዮች መረጃ ተላልፎ ይሰጥ ዘንድ ስምምነታቸውን እንዲገልጹ የሚጠየቅበት ሥልጣን

በHousing and Community Development Act፣ 1992፣ ሴክሽን 903ን መሠረት አድርጎ የተሻሻለው የStewart B. McKinney Homeless Assistance Amendments Act፣ 1988፣ ሴክሽን 904። ይህ ሕግ የሚገኘው 42 U.S.C. 3544 ላይ ነው።

በከፊል ሲታይ ይህ ሕግ እርስዎ ብቁ መሆን አለመሆንዎን ከመለየት ወይም የሚያገኙትን ጥቅም መጠን ከመወሰን ጋር በተያያዘ ደሞዝዎንና የሚያገኙትን ምንዳ ለማረጋገጥ ሲባል ባለቤቱ አሁን ያሉበትንም ሆነ በፊት የነበሩባቸውን ቀጣሪዎች እንዲጠይቅ ፈቃድ የሚሰጥ ነው። በተጨማሪም የHUD ደንቦች (24 CFR 5.659፣ የቤተሰብ መረጃና ማረጋገጫ) የመኖሪያ ቤት እገዛ ተጠቃሚ ለመሆን በቅድሚያ ብቁ መሆን አለመሆንዎን እንዲሁም የሚያገኙትን ጥቅም መጠን ለመወሰን ሲባል ማንኛውንም ተቀማጭም ሆነ የግል የገቢ ምንጭ በተመለከተ በHUD ዘንድ ተቀባይነት ያለውን የመረጃ ልቀት እና ስምምነት ቅጽ መፈረም እንደሚያስፈልግ ይደነግጋሉ። ይህም እርስዎ የሰጡትንና በሚከፍሉት ኪራይ መጠን ላይ ለውጥ የሚያመጣውን መረጃ ያካትታል። መረጃው እንደ ደሞዝ፣ የማኅበራዊ ደህንነት ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሁም ከተቀማጭ ሂሳብ የሚገኝ ወለድ የመሳሰሉትን ገቢና እሴቶች ይጨምራል። በተጨማሪም የቤቱ አባወራ ወይም የትዳር ጓደኛ የአቅም ገደብ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው አረጋዊ በሚሆኑበት ጊዜ በጥገኝነት ላሉትና ለቤተሰቡ የሚሠጡትን አበሎች እንዲሁም የልጆች እንክብካቤ ወጪን፣ የሕክምና ወጪዎችንና የአቅም ገደብ እገዛ ወጪዎችን በመሳሰሉ ገቢዎች ላይ ማስተካከያ ማድረግን ይጨምራል።

### መረጃው ተላልፎ እንዲሰጥ ስምምነት የሚጠየቅበት ዓላማ

ይህን የስምምነት ቅጽ ሲፈርሙ እገዛ ለማግኘት ማመልከቻ ያስገቡበት የመኖሪያ ቤቶች ፕሮጀክት ባለቤት እርስዎን በተመለከተ ከሦስተኛ ወገን መረጃ እንዲጠይቅ መፍቀድዎ ነው። HUD እገዛ የሚደረግባቸውን እነዚህን መኖሪያዎች ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆንዎን ለማወቅ እንዲሁም እገዛው በትክክለኛ መጠን መሰጠቱን ለማረጋገጥ ሲል ከዚሁ ጋር በተያያዘ እርስዎ የሰጧቸውን መረጃዎች የቤቱ ባለቤት እንዲያረጋግጥ ይጠይቃል። በHUD ቢሮ ወይም በPHA (እንደ ኮንትራት አስተዳዳሪ) በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የመኖሪያዎቹ ባለቤት ለHUD ወይም ለPHA በዚህ ስምምነት መሠረት እርስዎ የሰጡትን መረጃ አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል።

#### የሚገኘው መረጃ አጠቃቀም

በማረጋገጫው ቅጽ ላይ የተዘረዘሩት ግለሰቦች በማረጋገጫው ላይ የተጠየቀውን መረጃ በዚህ ቅጽ ላይ በተጠቀሰው ገደብ መሠረት መጠየቅ እና ማግኘት ይችሉ ይሆናል። HUD በእጁ ያስገባውን የገቢ መረጃ በPrivacy Act of 1974, 5 U.S.C. 552a የማስጠበቅ ኃላፊነት ይኖርበታል። ባለቤቱ እና PHAም እንዲሁ አግባብነት ባለው ማንኛውም የግዛቱ የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ መሠረት በእጃቸው የገባውን የገቢ መረጃ ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል። ባለቤቱ ከሦስተኛ ወገን የደረሰው መረጃ እርስዎ ከሰጡት የተለየ ሆኖ ከተገኘ ባለቤቱ መረጃው ትክክል እንዳልሆነ ለይቶ በማመልከት በጽሑፍ ሊያሳውቅዎ ይገባል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ከባለቤቱ ጋር ተገናኝተው ልዩነቱን ለማስታረቅ የሚችሉበት አጋጣሚ ይሰጥዎታል።

#### የስምምነት ቅጹን መፈረም ያለበት ማን ነው?

እድሜው ቢያንስ 18 ዓመት የሞላው እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተሰብ ራስ፣ የትዳር ጓደኛ፣ የኑሮ አጋር እድሜያቸው ምንም ይሁን ምን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመጀመሪያው ማረጋገጫ ወቅትም ሆነ በእያንዳንዱ የድጋሚ ማረጋገጫና ጊዜያዊ ማረጋገጫ ሂደት ወቅት አግባብ ያላቸውን የስምምነት ቅጾች መፈረም ይኖርባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ለአካለ መጠን የደረሰ አዲስ ሰው ቤተሰቡን ሲቀላቀል ወይም ከቤተሰቡ አባላት መካከል 18 ዓመት የሞላው ሰው በሚኖርበት ጊዜ እነርሱም አግባብ ያለውን የስምምነት ቅጽ መፈረም ይጠበቅባቸዋል።

በሚከተሉት ፕሮግራሞች እገዛ ለማግኘት የሚያመለክቱ ወይም እገዛ የሚያገኙ ግለሰቦች አግባብነት ያላቸውን የስምምነት ቅጾች መፈረም ይጠበቅባቸዋል፡-

የኪራይ እገዛ ፕሮግራም (Rental Assistance Program (RAP))

የኪራይ ድጎማ (Rent Supplement)

ሴክሽን 8 የመኖሪያ ቤቶች እገዛ ክፍያ ፕሮግራሞች (በቤቶች አስተዳደር ቢሮ የሚካሄድ) (Section 8 Housing Assistance Payments Programs (administered by the Office of Housing))

ሴክሽን 202 (Section 202)

ሴክሽን 202 እና 811 PRAC (Sections 202 and 811 PRAC)

ሴክሽን 202/162 PAC (Section 202/162 PAC)

ሴክሽን 221(ዲ)(3) ከገበያ ወለድ ተመን በታች (Section 221(d)(3) Below Market Interest Rate)

ሴክሽን 236 (Section 236)

HOPE 2 የባለብዙ ቤተሰብ ዩኒት የቤት ባለቤትነት (HOPE 2 Home Ownership of Multifamily Units)

## የስምምነት ቅጹን ሳይፈርሙ መቅረት

እንዲፈርሙ የሚፈለግብዎትን ማንኛውም የስምምነት ቅጽ ሳይፈርሙ መቅረት እገዛውን ሊያስከለክል ወይም የሚያገኙት የመኖሪያ ቤት እገዛ እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል። አንድ አመልካች በዚሁ ምክንያት እገዛውን እንዳያገኝ ከተከለከለ O/A በHandbook 4350.3 Rev. 1 ላይ የሰፈረውን የአሠራር ሂደት መከተል ይኖርበታል። አንድ ተከራይ በዚሁ ምክንያት እገዛውን እንዳያገኝ ከተከለከለ O/A በኪራይ ውሉ ላይ ያለውን የአሠራር ሂደት መከተል ይኖርበታል።

## ግዴታዎች

O/A የሚከተሉትን ነገሮች በተናጠል እስኪያረጋግጥ ድረስ ይህን ስምምነት መሠረት በማድረግ ስለ እርስዎ የተገኘውን መረጃ ተመርኩዞ ቤተሰብዎ የሚያገኘውን እገዛ ለማቋረጥ፣ ለመከልከል፣ ለጊዜው ለማቆም ወይም ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃ አይኖርም:- 1) ብቁ ከመሆንዎና ከሚያገኙት እገዛ መጠን ጋር በተያያዘ የሰጡት መረጃ እንዲሁም 2) ገቢን በተመለከተ (በሥራም ሆነ በሌላ መንገድ የተገኘ ገቢ) O/A እንደነዚህ ያሉትን ገቢዎች፣ ምንዳዎች ወይም ጥቅሞች እንደሚያገኙ (አግኝተው) ለራስዎ ጥቅም ያዋሉ መሆኑን እንዲሁም እነዚህን ገቢዎች፣ ምንዳዎች ወይም ጥቅሞች ያገኙበት ወቅት ወይም ከምን ጋር በተያያዘ እንዳገኙ ያረጋግጣል።

በግለሰብ የስምምነት ቅጹ ላይ በፊርማዎ የፈቀዱትን መረጃ ለመጠየቅ ሲባል የተፈረመው ስምምነት ቅጽ ፎቶ ኮፒ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ይህ የሚሆነው O/A የዋናው ቅጂ ፊርማ ያረፈበት ሌላ የግለሰብ ማረጋገጫ ስምምነት ከሌለውና O/A ለማረጋገጥ ሲል ሌላ ጥያቄ ማቅረብ የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ (ለምሳሌ፣ ሦስተኛ ወገን ምላሽ ሳይሰጥ ሲቀር) ነው። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከተከሰተ O/A የዚህን ስምምነት ቅጽ አንድ ፎቶ ኮፒ ከፈረሙበት የግለሰብ ማረጋገጫ ቅጹ ጋር ያያይዘዋል። ፎቶ ኮፒዎችን መጠቀም ለማስወገድ ሲባል ከሚያስፈልገው ከእያንዳንዱ የስምምነት ዓይነት ከአንድ በላይ ቅጽ ለመፈረም O/A እና ግለሰቡ ሊስማሙ ይችላሉ። O/A በዚህ ስምምነት አማካኝነት በተረጋገጠው መረጃ መሠረት የተገኘውን ውጤት ለእርስዎ ወይም እርስዎ ለወከሉት ሦስተኛ ወገን ያሳውቃል እንዲሁም በHandbook 4350.3 Rev. 1 መሠረት በዚህ ውጤት ላይ ተቃውሞዎን ማሰማት የሚችሉበትን አጋጣሚ ይሰጥዎታል።

O/A በግዛቱ የግል ገበና አጠባበቅ ሕግ መሠረት በዚህ ስምምነት አማካኝነት የተገኘውን መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

የስምምነት ቅጹን መፈረም ከሚጠበቅባቸው የቤተሰቡ አባላት መካከል አንዱ በቂ ምክንያት ኖሮ በወቅቱ መፈረም ሳይችል ቢቀር O/A የዘገየበትን ምክንያት እንዲሁም ፊርማውን በተቻለ ፍጥነት ለማግኘት የወጣውን እቅድ አስፍሮ መዝገቡን ይይዛል።

መረጃ ይፋ እንዲሆን የተሰጠው ስምምነት ከተፈረመ ከ15 ወር በኋላ አያገለግልም። O/A እነዚህን የግለሰብ የስምምነት ቅጾች የሚጠቀምባቸው ከማረጋገጫው ጊዜ በፊት ባሉት 120 ቀናት ውስጥ ነው። በተጨማሪም O/A እነዚህን ቅጾች በማረጋገጫው ሂደት ወቅት ሊጠቀምባቸው ይችላል። ሆኖም ይህ የሚሆነው O/A እርስዎ የሰጡት መረጃ ትክክለኛ እንዳልሆነ ሲገለጽለት ብቻ ነው። በሌላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል የተከለከለ ነው።

O/A ወጥ ያልሆነ መረጃ ካልደረሰው እንዲሁ የሰጡት መረጃ የተሳሳተ ነው ብሎ እንዲያምን የሚያደርገው ምክንያት ከሌለ በቀር 12 ወር በላይ የሆነውን መረጃ በተመለከተ ጥያቄ አያቀርብም። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመ O/A እገዛ ያገኙበትን ያለፉትን 5 ዓመታት መረጃ ሊሰበስብ ይችላል።

**ይህንን መረጃ ያነበብኩና የሚረጋገጠው መረጃ የሚወሰድበትን ዓላማና አጠቃቀሙን የተረዳሁ መሆኔን እንዲሁም መረጃው ለተጠቀሰው ዓላማና አገልግሎት ይፋ እንዲደረግ የተስማማሁ መሆኔን እገልጻለሁ።**

**የዚህን ስምምነት ዓላማ እና አጠቃቀም ያነበብኩና የተረዳሁ ሲሆን ስምምነቱን አላግባብ መጠቀም በግል ቅጣት እንደሚያስከትልብኝ የተገነዘብኩ መሆኔን እገልጻለሁ።**

**“የሚፈረመው የኪራይ ውሉ የእንግሊዝኛ ቅጂ ብቻ ነው።”**

## ይህን ስምምነት አላግባብ መጠቀም የሚያስከትለው ቅጣት:-

HUD፣ O/A እና ማንኛውም PHA (ወይም ማንኛውም የHUD፣ O/A ወይም PHA ተቀጣሪ) በዚህ ስምምነት መሠረት የተሰበሰበውን መረጃ ያለ ፈቃድ ይፋ አድርጎ ወይም አላግባብ ተጠቅሞ ቢገኝ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል።

በቅጽ HUD 9887-A መሠረት የተሰበሰበው መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው በቅጽ HUD 9887-A ላይ ለተጠቀሱት ዓላማዎች ብቻ ነው። አንድን አመልካች ወይም ተከራይ የተመለከቱ መረጃዎችን በሐሰት እያወቀ ወይም ሆነ ብሎ የሚጠይቅ፣ የሚወስድ ወይም ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ ሕግ በመተላለፍ የሚከሰስ ሲሆን ከ5,000 ዶላር የማይበልጥ ቅጣት ይጣልበታል።

በግዴለሽነት መረጃው ይፋ በመደረጉ የተበደለ ማንኛውም አመልካች ወይም ተከራይ ለደረሰው ጉዳት በHUD ሹም ወይም ሠራተኛ፣ በባለቤቱ እና ወኪሉ(O/A) ወይም መረጃው አላግባብ ይፋ እንዲሆን ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ባደረገው PHA ላይ የፍትሐ ብሔር ወይም ሌላ ተገቢ ሆኖ የተገኘው እርምጃ እንዲወሰድ መጠየቅ ይችላል።